# Learning by Ear 2013

## መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE SIX: የምስራች፣ የምስራች!

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Yann Durand**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: END OF THE SCHOOL DAY AT BONGO ACADEMY**

- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ምህረት (F, 15)**

**SCENE 2: ጃለታ AND ወይዘሮ ዘውዲቱ DISCUSS NIKI AT HOME**

- **ጃለታ (M, 45)**
- **ወይዘሮ ዘውዲቱ (F, 35)**

**SCENE 3: ምህረት ARRIVES HOME FROM SCHOOL**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ሉሊት (F, 40)**

**SCENE 4: ትዕግስት AND ዳንኤል MEET DOWNTOWN**

- **ዳንኤል (M, 15)**
- **ትዕግስት (M, 15)**

1. **<u>INTRO - NARRATOR:</u>**

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉን ተከታታይ ትምህርታዊ ድራማ ይዘን ቀርበናል። ዛሬ የሚደመጠዉ ስድስተኛ ክፍል ጭዉዉት “የምስራች፣ የምስራች” ይሰኛል። በዚህ ክፍል አዲስ ትምህርት ቤት የገቡትን ምህረት፣ ንጉሴ እና ዳንኤልን እንከታተላለን። ባለፈው ክፍል ጭውውት የሆነውን እናስታውስ

የምህረት እናት ህጻን ሴት ልጅ ብትወልድም ቤተሰቡ ሌላ ተጨማሪ ሰዉ መመገብ ስለማይችል በማለት የሉሊት ባል ሙላቱ ልጅቷን ሊወስድባት ፈልጓል፡፡

2. ሙላቱ (EP 05, 106): ሉሊት፣ ህጻኗን ስጪኝ…

3. ሉሊት: “እባክህን ያንን አታድርግ፡፡ ህጻኗ መጀመሪያ መመገብ ይኖርባታል፡፡ ስለዚህ ለእኔ ግዜ ስጠኝ፡፡ ”

4. ሙላቱ (111): “ በደንብ አድምጪኝ፡፡ ሴዳ ወይም ሌላ ሰው ስለ ህጻኗ ቢጠይቅሽ ከተወለደች ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ መሞቷን ንገሪያቸው፡፡ ተሳስተሽ የማደርገውን ነገር ብትነግሪያቸው …እመኚኝ ይቆጭሻል!”

ይህ በእንዲህ እንዳለ ትምህርት ቤት ያለችዉ ልጃቸው ምህረት እቤት ውስጥ ምን እደፈጠረ ምንም የምታዉቀዉ ነገር አልነበረም፡፡ በእርግጥ አስደሳች የሆነ የምስራች ገጥሟታል፡፡ ዳንኤል እና ንጉሴም ከፍተኛ ትኩረታቸውን ጥለውባታል፡፡ ጓደኛዋ ትዕግስትም ከራሷ ከምህረት በላይ በነገሩ የተደነቀች ይመስላል፡፡

5. ትዕግስት (EP 05, 85): ”ምህረት፣ ውቢት! ያጋጠመሽ አስደሳች ችግር ነው። ክፍላችን ካሉ ሁለት ቆንጆ ቆንጆ ወንዶች ሁለት የፍቅር ደብዳቤዎች! እድለኛ አይደለሽ? ”

6. ምህረት: ”እኔ ደግሞ እኔ ባልሆንኩ ኖሮ ብዬ ተመኘሁ። ”

ስለዚህ እዚያው ቦንጎ አካዳሚ ውስጥ ታሪኩን እንጀምራለን ። የዕለቱ ትምህርት ሊጠናቀቅ በመቃረቡ ምህረት፤ ዳንኤል እና ንጉሴ ምን እንደጻፉላት ልታይ ነው።

**<u>SCENE 1: END OF THE SCHOOL DAY AT BONGO ACADEMY</u>**

**7. SFX: SCHOOL BELL RINGS FOLLOWED BY STUDENTS LEAVING CLASS AND WALKING ALONG THE CORRIDOR**

**KW BEGIN**

8. ትዕግስት: ምህረት፣ ግን በጣም ትገርሚያለሽ ። ይህ ሁሉ ነገር ሲከሰት አንቺ ምንም አልመሰልሽም። ማለቴ ሁለት ወንዶች በአንቺ ፍቅር ሊተናነቁ ሲዘጋጁ አንቺ ግን ምንም ግድ የሌለሽ ነው የምትመስዪው ።

9. ምህረት: ባክሽ፣ ትዕግስት፣ እንደእዚያ አይመስለኝም። እንደማንኛውም ሰው ሊቀልዱብኝ ነዉ የፈለጉት፤ ከእዝያ ደግሞ መሳቅያ ሊያደርጉኝ ነዉ፡ ፡

10. ትዕግስት: ይልቅ ደብዳቤዎቹን እንክፈታቸው፡፡ ምን እንደጻፉ ማየት ጓጉቻለሁ! ግን ታውቂያለሽ፣ ምረጪ ብትይኝ፣ ንጉሴን ነው የምልሽ! እርሱ የመጨረሻ አሪፍና ማራኪ ልጅ ነው፡፡ በእዛ ላይ...የክፍላችን አለቃ ነው፡፡

**KW END**

11. ምህረት: አላውቅም፣ ትዕግስት...ይሄውልሽ! ብትፈልጊ ደብዳቤዎቹን አንቺ ክፈቻቸው!

12. **SFX: PAPER RUSTLE OF TWO ENVELOPES BEING HELD**

13. ትዕግስት: (surprised) እኔ? እኔማ አልችልም፡፡ ያንቺ ደብዳቤዎች ናቸው እ!

14. ምህረት: እባክሽን፣ በይ ክፈቻቸው! አጠገባችን እንደሆነ ማንም የለም፡፡

15. ትዕግስት: እሺ... ቆይ ወይኔ ጉዴ ፣ ተንቀጠቀጥኩ!እ,,, ንጉሴ ስለሚመቸኝ ከንጉሴ ደብዳቤ እጀምራለሁ፡፡

16. **SFX: LETTER BEING RIPPED OPEN**

17. **SFX: LETTER BEING UNFOLDED**

18. ምህረት: ድምጽሽን ከፍ አድርገሽ አንብቢው!

**19. ትዕግስት:** እሺ፣ እንግዲያው ስሚ፤ "የእኔ ውድ ምህረት፡፡ ከየት እንደምጀምር አላውቅም? ስሜቴን ለመግለጽ ቃላት ስፈልግ ነበር፡፡ መጀመሪያ ያየሁሽ ጊዜ የትምህርት ቤቱ መግቢያ በር ላይ ከጥበቃ ጋር ቆመሽ ነበር፡፡ ምንም እንኳን የለበስሽው እንዲያ የተቦጫጨቀ ጸጉርሽም በወጉ ያልሰራ ቢሆንም እኔ ግን በወቅቱ አንዲት የምታምር ሴት ልጅ ነበር ያየሁት፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከልቤ አልጠፋሽም፡፡ ምንአልባት ምን አይነቱ ደነዝ ነገር ነው ብለሽ ልታስቢኝ ብትችይም ልክ ልትሆኚ ትችያለሽ፣ ግን የደነዘኩት በአንቺ ፍቅር ነው፡፡"

**20. ምህረት:** (breaks out in huge laughter) በጣም ያስቃል!

**21. ትዕግስት:** ለኔ ግን በጣም በፍቅር የተሞላ ደብዳቤ ነው! እ,እ,,,ማንበቤን ልቀጥል?

**22. ምህረት:** አዎ፣ አዎ! ቀጥይ! ግን ፍጠኝ፣ በነዚህ ተራ ደብዳቤዎች የተነሳ ዘግይቼ ቤት መድረስ አልፈልግም፡፡ እናቴ ዛሬ በማንኛውም ሰዓት ልትወልድ ስለምትችል እርዳታዬ ያስፈልጋታል፡፡

**23. ትዕግስት:** (continues reading) "የምጠይቅሽ ምን ያህል እንደምወድሽ እንዳሳይሽ እድል እንድትሰጪኝ ብቻ ነው፡፡ እንዲህ ካደረግሽልኝ በዓለም ላይ የመጨረሻ ደስተኛ ወንድ እሆናለሁ! አሁን እንኳን ይህንን ደብዳቤ ጽፌ ጨርሼም ስለአንቺ እያሰብኩ ነው፡፡ ደብዳቤዉን ያሸኩት በከንፈሬ ስሜ ነው-ንጉሴ ጃለታ"

**24. ምህረት:** ስሜ አሸግኩት? (disgusted) እውይይይይ፣ እንዴት ያስጠላል!

25. **ትዕግስት:** (laughs out loud) ቆይ ቆይ ። ሌላም እኮ አለን

26. **SFX: LETTER BEING HANDED OVER**

27. **ትዕግስት:** እስኪ ዳንኤል ካሳሁን የንጉሴን ቅኔ መወድስ ይወዳደር እንደሆነ ደግሞ እንይ!

28. **SFX: LETTER BEING RIPPED OPEN**

29. **SFX: LETTER SPREAD OPEN**

30. **ምህረት:** እና …? ትዕግስት ምንድን ነው? የዳንኤልን ደብዳቤ ለምን አታነቢውም? የፈዘዝሽ ትመስያለሽ!

31. **ትዕግስት:** (disbelief) ይህንን አታምኚም፣ ምህረት! ይሄውልሽ እራስሽ እይዉ!

32. **ምህረት:** (also in disbelief) ወይኔ አምላኬ! ይህ ሁሉ ገንዘብ!

33. **ትዕግስት:** ዳንኤል የምሩን አንቺን መማረክ ፈልጓል። ትልቁ ጥያቄ ግን አሁን፤ እንዴት ልታደርጊ ነው?

34. **ምህረት:** (confused) ወይኔ… እኔ አላውቅም። ምን ማድረግ አለብኝ ትያለሽ፣ ቲጂ?

35. **ትዕግስት:** እውነተኛ መልሴን ትፈልጊያለሽ?

36. **ምህረት:** አዎን-አንቺ ጓደኛዬ ነሽ፣ ትዕግስት። የአንቺን እርዳታ እፈልጋለሁ።

37. **ትዕግስት:** እሺ፣ እንሂድ፤ እየሄድን እነግርሻለሁ።

38. **MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 2: ጃለታ AND MRS. ወይዘሮ ዘውዲቱ DISCUSS NIKI AT HOME**

**39. SFX: FOOTBALL MATCH GOING ON IN TV**

**40. ጃለታ:** **(reacts to match)** አአአሀ፣ ምን አይነት ተጫዋች ነው!

**41. ወይዘሮ ዘውዲቱ:** **(interrupts)** ጃለታ፣ መነጋገር ይገባናል።

**42. ጃለታ:** በኋላ ልንነጋገር አንችልም? የምወደውን ቡድን የእግር ኳስ ግጥምያ እያየሁ ነው።

**43. ወይዘሮ ዘውዲቱ:** አይመስለኝም። ንጉሴ ከትምህርት ቤት ከመመለሱ በፊት እንድንወያይበት እፈልጋለሁ።

**44. SFX: TV SET BEING SWITCHED OFF**

**45. ጃለታ:** ምንድን ነው ፤ ነገሩ? በዚህ ጊዜ ዉስጥ ንጉሴ ያላደረገው ምንድን ነው?

**46. ወይዘሮ ዘውዲቱ:** ስላላደረገው ነገር ሳይሆን እያደረገው ስላላ ጉዳይ ነው የምልህ።

**47. ጃለታ:** ፊጠን በያ ታዲያ ጨዋታው እያመለጠኝ እኮ ነዉ።

**48. ወይዘሮ ዘውዲቱ:** እንዴት እንደምነግርህ ግራ ገብቶኛል፤ እ,እ, ንጉሴ ኢንተርኔት ላይ የሚመለከተው…ይሄን እንዴት ብዬ ነው መግለፅ የምችለው … እ,እ,,, እንደሚመስለኝ ኢንተርኔት ውስጥ እርቃናቸውን የሆኑ ሴቶችን ይመለከታል።

**49. ጃለታ:** **(surprised)** ምን? ፖርኖግራፊ ማለትሽ ነዉ? ንጉሴ ፖርኖ እያየ ነው? እንዴት ልታዉቂ ቻልሽ?

50. ወይዘሮ ዘውዲቱ: ዛሬ ጠዋት ኮምፒዩተሩ ላይ አፍጥጦ ይዤዋለሁ፤ ከዝያም ምን እያደረገ እንደሆ እንዳላይ ከልክሎኝ ነበር፡፡ እንዳውም ከማየቴ በፊት ዘጋው፡፡

51. ጃለታ: ህምም፡፡ ይህ እማ ጥሩ አይደለም፡፡ ምን ማድረግ ያለብን ይመስልሻል ታድያ?

52. ወይዘሮ ዘውዲቱ: ምን ማድረግ እንዳለብን ትጠይቀኛለህ? አባቱ ነህ! እንደወንድ በግል ከተነጋገራችሁ አረጅም ጊዜ ይመስለኛል!

**KW BEGIN**

53. ጃለታ: እውነቱን ለመናገር ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፤ ስለትምህርት ቤት ጉዳይ ላናግረዉ ሞክሬያለሁ እሱ ግን ግልጽ ሊሆንልኝ አልፈለገም፡፡ በጣም ርቆኛል፡፡

54. ወይዘሮ ዘውዲቱ: አስተማሪዎቹን እናናግር እንዴ?

55. ጃለታ: አይሆንም! በፍጹም-ያንን ማድረግ የለብንም፡፡ ያ ልክ ቁሻሻ ሸማችንን መንገድ ላይ አዉጥተን እንደማስጣት ነው፡፡ ሌሎች ሰዎች ስለ ልጃችን መጥፎ ባህሪ ሲሰሙ ምን የሚያስቡ ይመስልሻል?

56. **ወይዘሮ ዘውዲቱ:** ይሁን እንግዲህ ፤ እኔዉ፣ እንደገና እጋፈጠዋለሁ። እንደ እዉነቱ ከሆነ ግን የሆነ ነገር ማድረግ አለብን። ይህ የማይሆን ልምድ ከስነምግባር ውጪ ነው የሚያደርገው።

**KW END**

57. **ጃለታ:** አትጨነቂ፣ የንጉሴ እናት፣ እኔ አናግረዋለሁ። ካስፈለገም፣ ኮምፒዩተሩን እነጥቀዋለሁ። አሁን በቃ፤ ጨዋታውን መከታተል እችላለሁ?

58. **ወይዘሮ ዘውዲቱ:** ኡ ኡ,,,,,አንተ እና አግርኳስህ! ያም ቢሆን የአባቱ ልጅ። ሁለታችሁም የቴሌቪዥን እና የኮምፒውተር ሱሰኞች!

59. **SFX: TV SWITCHED ON, MATCH CONTINUES**

60. **ወይዘሮ ዘውዲቱ:** ይህን ተራ ጨዋታ የፈጠረውን እንዴት ጠላሁት!

61. **MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: ምህረት ARRIVES HOME FROM SCHOOL</u>**

62. **SLUM ATMO**

63. **SFX: IRON SHEET DOOR BEING OPENED**

64. **SFX: FOOTSTEPS - ምህረት COMES IN**

65. **ምህረት:** **(calls out)** እማዬ፣ መጥቻለሁ።-እማ እንዴት ነሽ? **(sees her mother lying on the floor)**ወይኔ! ጉዴ! ምንድን ነው ጉዱ፤ ምንድን ነዉ የሆነዉ እዚህ? እማዬ…

66. **ሉሊት:** (faintly) ምህረት…ምህረት፣ በመምጣትሽ ተደስቻለሁ።

67. **ምህረት:** (utterly shocked) እማ! ብዙ ደም ፈስሶሻል።

68. **ሉሊት:** ምህረት፣ ትንሽ ታጸዳጂዉ? እኔ ትንሽ ማረፍ እፈልጋለሁ። በጣም ደክሞኛል።

69. **ምህረት:** (deeply concerned) ልጁ የታለ? ምን ሆነ ልጁ?

**KW BEGIN**

70. **ሉሊት:** (groaning in pain)

71. **ምህረት:** ብቻሽን ነው እንዴ የወለድሽው? አዋላጇ ወይዘሮ ሠዓዳ የታሉ?? እንዲመጡ ነግሬያቸዉ ነበር። አባዬስ ቢሆን እቤት መሆን አልነበረበትም?

72. **ሉሊት:** (faintly) ምህረት…ደክሞኛል። ስለ ተወለደዉ ህጻን አባትሽ ቤት ሲመጣ ያብራራልሻል። እባክሽን የምልሽን አድርጊ ቤቱንም አፀዳጂው።

73. **ምህረት:** አባዬ? እዚህ ካልነበረ እንዴት ሊያብራራልኝ ይችላል? (disbelief) ወይኔ አምላኬ! አባዬ እዚህ ነበር ማለትሽ ነው? ግራ እየገባኝ ነው፣ እማዬ። ልጁ የታለ?

**KW END**

74. **ሉሊት:** (Crying) ሞታለች። እንደ መጥፎ ህልም ነው የሚታየኝ። ምህረት፣ እባክሽ እርጂኝ።

75. SFX: ሉሊት BEING LIFTED OFF THE GROUND BY ምህረት WITH SOME DIFFICULTY

76. SFX: CLOTH RUSTLE

77. ምህረት: እማዬ፣ የሚረዳሽ ሰው ሄጄ ማምጣት አለብኝ። እዚህ ጋር አልጋው ላይ ዝም ብለሽ ጋደም በይ… ሐኪም ቤት ልንወስድሽ ያስፈልጋል።

78. ሉሊት: (faintly) አይሆንም! አትሂጂ፣ የእኔ ልጅ፤ እዚህ እንድትሆኚ፣ እፈልጋለሁ። እባክሽን፣ አትሂጂ… ብቻዬን መሆን አልፈልግም።

79. ምህረት: እማዬ፣ ባለሽበት ቆዪኝ- አሁኑኑ እመለሳለሁ።

80. SFX: FOOTSTEPS WALKING AWAY

81. SFX: IRON SHEET DOOR BEING OPENED

82. MUSIC INTERLUDE

<u>SCENE 3: ትዕግስት AND ዳንኤል MEETING DOWNTOWN</u>

83. SFX: TOWN ATMO IN THE EVENING

84. ዳንኤል: (calls out) ትዕግስት! ትዕግስት! ታዲያስ ……

85. ትዕግስት: (pleasantly surprised) ዳንኤል! ሰላም ሰላም! እዚህ ምን እያደረክ ነው? እየተከታተልከኝ ነበር እንዴ?

86. ዳንኤል: (trying to find words) እእእ,,,አረ አይደለም፣ ከተማው ውስጥ ዝም ብዬ እየተንሸራሸርኩ ነበር። በአጋጣሚ ነው ያየሁሽ፣

87. ትዕግስት: ለማንኛውም… (maliciously) ዳንኤል፤ ለምህረት የሰጠሃትን ነገር አይቼዋለሁ።

88. ዳንኤል: (shocked) አየሽው? እንዴት? መሆን የነበረበት ግን እኮ,,,, አ,,, ልክ ነዉ ፣ ጓደኞች ናችሁ ለካ። ታድያ አሳይታሽ መሆን አለበት።

89. ትዕግስት: ዳንኤል፣ ታውቃለህ ምህረት አትፈልግህም። ከአንተ ንጉሴ ይሻላታል። ንጉሴን እንደምትመርጥም በጣም እርግጠኛ ነኝ።

90. ዳንኤል: እንዴት አወቅሽ? እራሷ ነገረችሽ?

91. ትዕግስት: የልብ ጓደኛዋ ነኝ። ስለ ሁሉም ነገር ትነግረኛለች።

92. ዳንኤል: (heartbroken) ውሸት ነው! አላምንሽም። ስለዚህ ጉዳይ እራስዋ ነግራሻለች? ለኔ ያላትን አስተያየት አይቻለሁ። ስለ እኔ የሆነ ስሜት እንዳላትም አውቄያለሁ።

93. ትዕግስት: እና ለስዋ ገንዘብ በመስጠት የምትገዛት ይመስልሀል?

94. ዳንኤል: በፍጹም! ቤተሰቦቿ ድሆች እንደሆኑ አውቃለሁ። እንዲሁ በትንሹ ልረዳት ፈልጌ ነዉ። ግን በፍጹም በገንዘቤ እየገዛኋት አይደለም!

95. ትዕግስት: (sarcastic) እረ ባክህ፣ መልካም፤ እንዴት አይነት ቅን ነህ! አቶ ለጋስ!

96. ዳንኤል: (realizing) ቀንተሽ ነው! አሁን ገባኝ፤ ትዕግስት! ምህረት ላይ ቀንተሽባታል!

97. ትዕግስት: (defensive) ቅናት?ማን አባክህ እኔ? አይነካካኝም! እንዴት እንዲህ ልትል ቻልክ? በህይወቴ ብዙ ወንዶች ነበሩኝ፤ አሁን ደግሞ ፈጽሞ ማንንም አልፈልግም።

98. ዳንኤል: ምን አልሽ ምን አልሽ? ብዙ ወንዶች ነበሩኝ ነው ወይንስ በቂ ወንዶች አሉኝ ነው ያልሽው? አልገባኝም።

99. ትዕግስት: (seductive) ዳንኤል! ሁለታችን አንድ ላይ የመጨረሻ ልንጫጫስና ልንግባባ እንደምንችል ይሰማኛል፣ እኔ እና አንተን የሚያመሳስለን ብዙ ነገሮች አሉን። አይመስልህም?

100. ዳንኤል: (caught off guard) መልካም...ህምምም...ይቅርታ፣ ትዕግስት፣ ድንገት በመገናኘታችን ደስ ብሎኛል፤ አሁን ግን መሄድ አለብኝ። ምህረትን ቀድመሽኝ ካገኘሻት ሰላም በይልኝ። ቻዎ።

**KW BEGIN**

101. ትዕግስት: (still seductive) ዳንኤል፣ በዚህ ትልቅ ከተማ ውስጥ፤ አንዲት ሴት ልጅን ብቻዋን ጥለህ ትሄዳለህ፣? ለዝያዉም በዚህ ውድቅት ሌሊት?

**102. ዳንኤል:** (leaving, acting courteous) በፍጹም! በርግጥም ጥያት አልሄድም።. (sarcastic) ግን ይህች ልጅ ሲጀመርም በዚህ ውድቅት ሌሊት እዚህ ትልቅ ከተማ ውስጥ ብቻዋን ነበረች፣ ስለዚህ ከተማውን በደንብ የምታውቀው ይመስለኛል። መልካም ምሽት፣ ትዕግስት። መልካም የሳምንት መጨረሻ።ሰኞ ትምህርት ቤት እንገናኛለን።

**KW END**

**103. ትዕግስት:** (thinking to herself) እሺ ዳንኤል፤ ለማግኘት ብዙ መታገልን ትፈልጋለህ? ትዕግስት ማን እንደሆነች አሳይሀለሁ። ይህ ገና ጅማሬዩ ነው!

**104. MUSIC INTERLUDE**

**105. OUTRO - NARRATOR**

በዚሁ “መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ-ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ” በሚል የጀመርነዉን ተከታታይ ድራማ ክፍል ስድስት እናጠናቅቃለን። ትዕግስት የምትጫወተው ምን አይነት ጨዋታ ይሆን? አሁን ዳንኤልን መፈለጓን አሳይታዋለች፤ እርሱስ እንዴት ይመልስላት ይሆን? ይህስ በትዕግስት እና ምህረት ጓደኝነት ላይ ምን አይነት ተጽእኖ ይኖረዋል? የእነዚህንና ሌሎች ታሪኮችን በቀጣዩ ክፍል ጭዉዉት ይከታተሉ። የዛሬዉን ድራማ በድጋሚ ማድመጥ ከፈለጉ በድረ-ገጽ አድራሻችን dw.de/lbe ላይ ያገኙታል። ድራማዉን በግል ማኅደሮ ማስቀመጥ ከፈለጉ ከድረገፁ ላይ መገልበጥ ይችላሉ። በፌስ ቡክ ገጻችን ላይም ሊከታተሉን እንደሚችሉ አይዘንጉ። በቀጣዩ ክፍል እስክንገናኝ ድረስ ጤና ይስጥልን!